# በዲሲ (DC) ውስጥ የሚፈጸሙ የቤት ሁከትና ረብሻን( Domestic Violence) በተመለከተ ህጋዊ አገልግሎት ሰጪዎችና ቦታዎች

## አማራ (Amara)

አማራ (Amara) ገንዘብም ሆነ ሌላ ጠቀሜታ ለማግኘት በውዴታም ሆነ በአስገዳጅነት ወይም በተገኙበት ቦታና ሁናቴ ምክንያት የግብረ ስጋ ግኑኝነት ለተፈጸመባቸው ሕጋዊ ምክሩን የመስጠትና ወደ ሚመለከተው መስርያ ቤቶች የማስተለለፍ አገልግሎቱን አሁንም እየቀጠለ ነው። አማራ(Amara) በወቅቱ በአስቸኳይ የጥሪ መስመሩ: በስልክ ቁጥር (240) 257-6492 ጥሪ፡ በኢሜልም በ info@amaralegal.org እንዲሁም በዌብሳይቱም https://www.amaralegal.org/make-a-referral ጽሁፍ እየተቀበለና ጉዳዩ ወደሚመለከተው እያስተላለፈ ነው።

## አዩንዳ (Ayuda)

አዩንዳ(Ayuda) በየቀኑ ከጥዋቱ 9:00 ሰዓት እስከ ቀኑ 12:00 ሰዓት፡ ከሰኞ እስከ ዓርብ ስልክ የሚደወልበት ግዜ ሰጥቶ የስልክ -ጥሪዎችን እየተቀበለ ነው። ይሄው ዕለታዊ ጥሪ የመቀበል ጉዳይ በቤት ውስጥ ሁከትና ረብሻ (domestic violence) የደረሰባቸው፡ የወሲብ ግፍ (sexual assault )ና የድብያ (stalking) ግፍ የተፈጸመባቸው ስደተኞች፡ ከሲ-ፒ-ኦ (CPO )ሕጋዊ እርዳታ ቢፈልጉ፡ የቤተሰብ ሕጋዊ ጉዳዮችን በተመለከተ፣ ወንጀል ለተፈጸመባቸው ጥብቅና የመቆም ጉዳይና የጉዳይ አስተዳደርና ቴራፒ በሚመለከት እርዳታ ቢፈልጉ እርዳታ የሚያደርግ ነው። እነኚህ ስደተኞችም በስልክ ቁጥር(202) 387-4848 ደውለው ከላይ የተዘረዘሩትን አገልግሎቶች ሊያገኙ ይችላሉ።

## ዳቦ ለከተማ (ብሬድ ፎር ዘ ሲቲ-Bread for the City)

ዳቦ ለከተማ ወይም ብሬድ ፎር ዘ ሲቲ( Bread for the City) አዲስ የስልክ ጥሪዎችን እየተቀበለ ነው። የቤተሰብ ሕግን፡ የመኖርያ ቤት ጉዳይ፣ ህዝባዊ ጠቀሜታዎችን ወይም ኢሚግራሽን(ስደተኛነትን) በተመለከተ በስልክ ቁጥር 202-386-7616 ይደውሉና መልእክት ይተው፡ ከዛም አንድ ሰው መልሶ ይደውልሎታል።

## ብሬክ ዘ ሳይክል (Break the Cycle)

ብሬክ ዘ ሳይክል (Break the Cycle ) በሲቪሎች ጥበቃ ትእዛዝ ስር ( Civil Protection Order)፡ በልጅ አሳዳጊነት ትእዛዝ ስር( custody) እንዲሁም በልጆች ድጋፍ ጉዳዮች ውስጥ ላሉ ሰዎች ህጋዊ ምክር ለመስጠት የስልክ ጥሪ ይቀበላል። በወንጀል ምስክር ጥብቅና ስርም የጥብቅና ምክር፣ አስፈላጊ መረጃ እንዲሁም ታይትል IX (Title IX)እና በማህበራዊ አገልግሎት ጉዳዮች ላይ እገዛ እየሰጠ ነው። ይህ አገልግሎት ዕድሜአቸው ከ 12 – 24 ዓመት የሆኑና ከተቃራኒ ጾታ ጋር በሚደረግ ቀጠሮ ግፍ የተፈጸመባቸው (dating assault)፡ በወሲብ ግፍ፡ በቤት ውስጥ ሁካታና ረብሻ ውስጥ ያለፉ ወጣቶችን የሚያገለግል ነው። በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ምክር ወይም መረጃ ከፈለጉ በስልክ ቁጥር 202-849-6282 ይደውሉ ወይም ወደ legalservices@breakthecycle.org ኢሜል ያድረጉ።

## የዲሲ (DC )የፈቃደኛ ጠበቆች ፕሮጀክት (DC Volunteer Lawyers Project)

የዲሲ የፈቃደኛ ጠበቆች ፕሮጀክት (DCVLP) ከሰኞ እስከ ዓርብ ከጥዋቱ 9:00 ሰዓት እስከ 5:00 ሰዓት ከሰዓት በኋላ ህጋዊ ምክር በነጻ ካለ ምንም ክፍያ በስልክ እየሰጠ ነው። ይህ አገልግሎት በቤት ውስጥ ሁካታና ረብሻ ፡ በወሲብ ግፍ ፡ በድብያ የሚሰቃዩ ግለሰቦችንና አደጋ ላይ ላሉ ህጻናት ልጆች እንክብካቤ የሚያደርጉ ሰዎችን ይመለከታል። ወደዚህ የሚደውሉ ሰዎች የሲቪል ጥበቃ ትእዛዝን፡ የልጅ አሳዳጊነት ሕግን እንዲሁም ልጆችን ለመርዳት ስለሚደረግ እርዳታና ስለስደተኛነት አጭር ምክር ሊያገኙ ይችላሉ። ለዚህም በስልክ ቁጥር (202) 425-7573 ደውለው ወይም በኢሜል clinic@dcvlp.org ጽፈው ከህግ ጽሕፈት ቤቱ ጋር ሊገናኙ ይችላሉ።

## ዲቪ ሊፐ (DV LEAP)

ዲቪ ሊፐ (DV LEAP) በኦንላይን መስመሩ https://www.dvleap.org/application አቤቱታዎችን እየተቀበለ ነው።

**<u>ሕጋዊ ኤድ ሶሳይቲ (Legal Aid Society)</u>**

የዲሲ ሊጋል ኤድ ሶሳይቲ (The Legal Aid Society of D.C) የሲ-ፒ-ኦ (CPO)፣ በቤት ውስጥ የሚደረግ ረብሻና ሁከት የሚመለከት፣ የልጅ አሳዳጊነት፣ የልጅ ማሳደግያ እርዳታ፣ ፍቺ፣ የህዝብ ጠቀሜታዎች( ከስራ የመውጣት ኢንሹራንስ ጭምር) የቤትና ከመኖርያ ቤት የመባረር ጉዳይ፡ ቤት በወለድ-አገድ መያዝ ፡ ስደተኛነትን እንዲሁም የይግባኝ ጉዳዮችን በተመለከተ ህጋዊ ምክር በስልክ ይሰጣል። ለእነዚህ ጉዳዮች እርዳታ ለማግኘት በስልክ ቁጥር (202) 628-1161 ወይም ደግሞ ወደ https://www.legalaiddc.org/online-intake ገብተው ይጎብኙ።

**<u>ኤን-ቪ-አር-ዲ-ሲ (NVRDC)</u>**

ኤን-ቪ-አር-ዲ-ሲ (NVRDC) በስልክ ቁጥር (202) 742-1727 ከደወሉ አጭር ህጋዊ ምክር በመስጠትና ደዋዮችን ከጠበቃዎች ጋር በማገናኘት ይሰራል። ደዋዮች ከላይ በተጠቀሰው ስልክ ደውለው መልእክት ከተው የመልስ ጥሪ ያገኛሉ። ይሄው ድርጅት፡ የወሲብ ግፍ የተፈጸመባቸው ግለሰቦች ምርመራን ጉዳይ በተመለከተ አሁንም ከሓኪም ቤቶች ጋር ግንኙነቱን እየቀጠለ ነው። በላያቸው ላይ ወሲባዊ ግፍ የተፈጸመባቸው ግለሰቦች አገልግሎት ለማግኘት በስልክ ቁጥር 1-844-4HELPDC (1-844-443-5732) ይደውሉ ወይም በ ኢንተርኔት www.DCvictim.org/chat ገብተው ይወያዩ።

**<u>የሴፍ ሲስተርስ(የእህትማማቾች) ሰርክል (Safe Sisters Circle)</u>**

ይህ ሴፍ ሲስተርስ ሰርክል (Safe Sisters Circle) በሲቪሎች ጥበቃ ትእዛዝ (Civil Protection Order ) ውስጥ ያሉና የልጅ አሳዳጊ ጉዳዮችን በሚመለከቱ በስልክ አጭር ምክር የሚሰጥ ነው። ስለዚህ ጉዳይ መወያየት የፈለጉ ግለሰቦች በኢሜል info@safesisterscircle.org ሊጽፉ ወይም በስልክ ቁጥር (202) 596-5209 ሊደውሉ ይችላሉ።

**<u>የዲሲ ቪክትም ሊጋል ኔትወርክ ( Victim Legal Network of DC)</u>**

የዲሲ የተጎዱ ሰዎች ሕጋዊ ኔትወርክ (VLNDC) በስልክ ቁጥር (202) 629-1788 የተደወለለትን ጉዳዮች ይቀበላል። ደንበኞች በኦንላይንም፣ የጉዳይ መቀበያ ፎርም ከሞሉ በኋላ፡ ጉዳያቸውን ሊያቀርቡ ይችላሉ: https://vlndc.org/for-victims-of-crime/get-help/. የሲቪል ጥበቃ ትእዛዝ (Civil Protection Orders) ና ወንጀል ለተፈጸመባቸው እርዳታ የሚሰጥ ድርጅትን (Crime Victims Compensation) በሚመለከት አጭር ምክር ይሰጣል።